# እግዚአብሔር ልታውቃቸው የሚፈልገው አራት ነገሮች

1 2 3 4

1. መዳን አለብህ

ኢየሱስ “ዳግም መወለድ አለብህ” አለ።

ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያይ አይችልም። ዮሐ. 3፡3

ሁሉም ኃጢአትን ሰርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል። ሮሜ 3፡23

በምድር መልካምን የሚሰራ ኃጢአትንም የማያደርግ ፃድቅ አይገኝምና። መክ. 7፡20

ሁላችን እንደ እርኩስ ሰው ሆነናል፥
ፅድቃችንም ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው። ኢሳ. 64፡6

የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ እጅግም ክፉ ነው። ማንስ ያውቀዋል? ኤር. 17፡9

እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፥ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ። ኢሳ. 53፡6

2. ራስህን ማዳን አትችልም

እንደ ምህረቱ መጠን አዳነን እንጂ እኛ ስላደረግነው በፅድቅ ስለነበረው ስራ አይደለም። ቲቶ 3፡5

ስጋን የለበሰ ሁሉ በሕግ ስራ ስለማይፀድቅ፤ እኛ ራሳችን በህግ ስራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንፀድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል። ገላ. 2፡6

ህግን ሁሉ የሚጠብቀው ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለ ይሆናል። ያዕ. 2፡10

ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች፤ ፍፃሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው። ምሳ. 14፡12

ኢየሱስም፡- እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም። ዮሐ. 14፡6

3. ኢየሱስ አንተን ሊያድን ሞቶአል።

ለኃጢአት ሞተን ለፅድቅ እንድንኖር፤ እርሱ ራሱ በስጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ። 1 ጴጥ. 2፡24

ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ፃድቅ ሆኖ ስለ አምፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና። 1 ጴጥ. 3፡18

እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ፅድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው። 2 ቆሮ. 5፡21

በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። ዮሐ. 3፡16

4. ኢየሱስ በኃጢአት ላይ ድልን ይሰጣል በፈተናም እንድትፀና የደርግሃል።

ጌታ እግዚአብሔርን የሚያመልኩትን ከፈተና እንዴት እንዲያድን፤ በደለኞችንም ይልቁንም በእርኩስ ምኞት የስጋን ፍትወት እየተከተሉ የሚመላለሱትን ጌትነትንም የሚንቁትን እየቀጣቸው ለፍርድ ቀን እንዴት እንደሚጠበቅ ያውቃል። 2 ጴጥ. 2፡9

ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው። ትታገሱም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል። 1 ቆሮ. 10፡13

እንግዲህ ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ። ዮሐ. 8፡36

ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፥ አሮጌው ነገር አልፏል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗል። 2 ቆሮ. 5፡17

## አንተ ማድረግ ያለብህ።

### በእግዚአብሔር ቃል እመን።

ቃልህ እውነት ነው። ዮሐ. 17፥17

አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግስት ፅድቁንም ፈልጉ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል። ማቴ. 6፥33

ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል። ማር. 8፥36

እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት ቀርቦም ሳለ ጥሩት። ኢሳ. 55፥6

እነሆ የመዳን ቀን አሁን ነው። 2 ቆሮ. 6፥2

ቀን የሚያመጣው ምን እንደሆነ አታውቅምና፤ ነገ በሚሆነው አትመካ። ምሳ. 27፥2

እኛስ እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንለው እንዴት እናመልጣለን። ዕብ. 2፥3

## አሁኑኑ አድርገው።

### ንሰሐ ግባ። (ከኃጢአትህም ተመለስ)

ነገር ግን ንሰኃ ባትገቡ እንዲሁ ትጠፋላችሁ። ሉቃ. 13፥3

### ኃጢአትህን ለክርስቶስ ተናዘዝ።

አንድ እግዚአብሔር አለና፤ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፤ እርሱም ሰው የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። 1 ጢሞ. 2፥5

በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ። ሐዋ. 16፥31

### ኢየሱስ አዳኝ መሆኑን ለሰዎች መስክር።

ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሳው በልብህ ብታምን ትድናለህ። ሮሜ 10፥9

## አስታውስ!

እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን። ሮሜ 14፥12

ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደተመደበላቸው። ዕብ. 9፥27

ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን ወደ ፍርድ አይመጣም። ዮሐ. 5፥24

### የምታመልከውን ዛሬ ምረጥ።

ኃጢአተኛ መሆኔን በመገንዘብና ኢየሱስ ለኃጢአተኞች እንደሞተ በማወቅ አሁን ኢየሱስን እንደ ግል መድኃኒቴ ተቀብዬዋለሁ።

—————————//————————

ተጨማሪ ሃሳብ ሆነ እርዳታ ከፈለጉ ወይም ጥያቄ ቢኖርዎት በስልክም ሆነ በደብዳቤ ወይም በግል መጥተው ያነጋግሩን። እርስዎን ማገልገል ዋናው ተግባራችን ነው።


አድራሻችን

Amanuel Ethiopian Church
3300 Wilshire Blvd.
Los Angeles CA 90010

Tel. (213) 381-0060
e-mail:- amanuel4la@aol.com